የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ዘጠናኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No 34
ADDIS ABABA 30th August, 2023

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፴፰/፪ሺ፲፭

ሽልድቫክስ ኢንተርፕራይዝን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……...................................ገጽ ፲፬ሺ፰፻፹፩

## Content

Regulation No. 538/2023

Council of Ministers Regulation to the Establishement of the Shieldvax Enterprise………………………….......Page 14881

**ደንብ ቁጥር ፭፻፴፰/፪ሺ፲፭**

**<u>ሽልድቫክስ ኢንተርፕራይዝን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀፅ ፵፯ (፩) (ሀ) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

**ይህ ደንብ " ሽልድቫክስ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፴፰/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡**

**፪. መቋቋም**

፩/ ሽልድቫክስ ኢንተርፕራይዝ ከዚህ በኋላ ኢንተርፕራይዙ እየተባለ የሚጠራ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**REGULATION NO 538/2023**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO THE ESTABLISHMENT OF THE SHIELDVAX ENTERPRISE**

This regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1984.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "ShieldVax Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No 538/2023."

**2. Establishment.**

1/ The ShieldVax Enterprise ("hereinafter referred as the Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

፪/ ኢንተርፕራይዙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**፫. ተጠሪነት**

የኢንተርፕራይዙ ተጠሪነት ለኢትዮ-ባዮፋርማ ግሩፕ ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንተርፕራይዙ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የሀገሪቷ ክፍሎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊከፍት ይችላል፡፡

**፭. ዓላማ**

ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ ክትባቶችንና ተዛማጅ ምርቶችን በማምረት ብሔራዊ የጤና ደህንነትን መጠበቅ፤

፪/ ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ክትባቶችን በማምረት የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ማሟላት፤ የገቢ ምርቶቹን መተካት እና ወደ ውጪ ገበያ በመላክ የውጪ ምንዛሬን ማሳደግ፤

፫/ በክትባት ማበልጸግና ማምረት ዘርፍ የሚደረግ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማሳለጥ የሀገርን አቅም በመገንባት ሊከሰቱ ለሚችሉ ወረርሽኞች ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣ መከላከልና መቆጣጠር፡፡

**፮. ተግባርና ኃላፊነት**

ኢንተርፕራይዙ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ ለተለያዩ የሰው በሽታዎች ዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸውን ክትባቶች እና ግብአቶች ማምረት፣

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**3. Accountability**

The Enterprise shall be accountable to Ethio-Biopharma Group.

**4. Head Office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and it can open branch in other parts of the country as may be necessary.

**5. Objective**

The objectives for which the enterprise was established are as follows:-

1/ Protect the national health security by manufacturing vaccines and other affiliated products;

2/ Increase foreign currency by filling local demand by manufacturing vaccines of international quality to substitute the imported goods while exporting them;

3/ Build the capacity of local institutes by facilitating technology transfer in the field of vaccine enrichment for response and preparedness during possible epidemics and pandemic ;

**6. Duty and Responsibility**

The Enterprise shall have the following duties and responsibilities are:

1/ Produces internationally quality assured vaccines and ingredients for various human diseases;

፪/ ለምርምር ሥራ እና ለመሰል አምራች ተቋማት የሚያገለግሉ ሪኤጀንቶችን ማምረት፤

፫/ ክትባቶች እና ግብአቶችን ማበልጸግ፤

፬/ ለሀገር ውስጥ እና ለውጪ የክትባት አበልጻጊዎች የማምረት አገልግሎት መስጠት፤

፭/ ምርቶችን ለሀገር ውስጥ እና ለውጪ ገበያ ማቅረብ፤

፮/ በክትባት ማበልጸግና ማምረት ሥራ የዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማከናወን፤

፯/ የተቋቋመበትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

## ፯. ካፒታል

የኢንተርፕራይዙ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፯ ቢሊዮን (ሰባት ቢሊዮን ብር) ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ፩ ቢሊዮን ፯፻፶ ሚሊዮን (አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

## ፰. ኃላፊነት

ኢንተርፕራይዙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ፱. የቆይታ ጊዜ

ኢንተርፕራይዙ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

2/ Manufacture reagents used as input for similar manufacturers and research institutes;

3/ Develops vaccines and input materials;

4/ Provides manufacturing services for local and foreign vaccine product developers ;

5/ Supplies products to domestic and foreign markets;

6/ Transfer of knowledge and technology in vaccine development and production;

7/ To engage in any other related activities as are necessary for the attainment of its objectives.

## 7. Capital

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 7,000.000,000 (Seven Billion) of which 1,750,000,000 (One Billion Seven Hundred Fifty Million Birr) is paid up in cash and in kind.

## 8. Liability

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

## 9. Duration

The Enterprise is established for an indefinite duration.

**፲. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቲር**

**10. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, on this 30th Day of August, 2023.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**